የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

# ወያኔ በሕዝብ ላይ የሚፈጽመውን ግፍና ግድያ እናውግዝ

**ከኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ**

**የተሰጠ መግለጫ ታህሳስ 13/2008**

ጨቋኙ የወያኔ አገዛዝ በቅርቡ ተቀስቅሶ ያለውን የሕዝብ ተቃውሞ ለማፈን ሲጥር በርካታ ንጹህ ዜጎችን መግደሉ በይፋ ተነግሯል ። ጸረ ሰላም ሀይሎች በሚል በተለመደው ሽፋኑ ተቃዋሚዎችን ከሶ ግድያቸውንም ማጠየቂያ ሊሰጥ መሞከሩንም ዜጎች ሁሉ የታዘቡት ነው ። በርካታ ዜጎችንም ታግተው ስየል እየተቀበሉ ናቸው ። ይህን ሁሉ ግፍና ግድያ ኢፖእአኮ አጥብቆ ያወግዛል ።

ከአምቦ እስከ ሀሮማያ፤ ከጅማ እስከ ጎንደር፤ ጋምቤላ፤ ዋልድባ ፤ኦጋዴን፤ወዘተ ዜጎች የወያኔ የግፍ በትር እየመታቸው ነው ። የአዲስ አበባ መስፋፋት ወይም ማስተር ፕላን ብሎ አገዛዙ ያመጣውን ዕቅድ ተቃውሞ ያሰሙ ዜጎች ሲጠቁ ይህ የመጀመሪያው አይደለም ። ገዢው ክፍል የሕዝብ መሬት እየነጠቀና ለባዕድ እየሰጠ ወይም እየሸጠ በዚያውም ሺዎችን እያፈናቀለ የቆየ ነው ። የግዳጅ ሰፈራም ከተጀመረ ዓመታት አልፈዋል ። አገዛዙ ሰፊ የሙብት ረገጣ ሲያደርግ ከሃያ አመታት በላይ ሆኖታል ። በሀይማኖት ጉዳይም ጣልቃ እየገባ ምዕመናን እየጎዳ ነው --አደባባይ ኢየሱስ፤አንዋር መስጊድ፤ ለእስር የተዳረጉና የተገደሉ የሀይማኖት መሪዎችና ተከታዮች ምስክር ናቸው ። በቃሊቲ፤ ቂሊንጦ፤ ዝዋይ፤ ወዘተ ስንቱ የፖለቲካ እስረኛ መከራ እያየ ነው ። ስየል የተለመደና የተስፋፋ ነው፤ ፍትህ ደብዛዋ ከጠፋ ዓመታት አልፈዋል፤ ፍትሃዊ አተዳደር የህልም እንጀራ እንደሆነ አለ ። በዚህ በዚያ ተቃውሞ በተከሰተበት ሁሉ አገዛዙ ግድያና አፈና እያካሄደ ነው ያለው ። ግርግር ለሌባ ያመቻል እንዲሉ በዚሁ ሰበብ ደግሞ የጥላቻ በሽታቸውን ለማከም ንጹህ ህዝብን የተወሰነ ብሄረሰብ አባል በሚል ግድያ የሚፈጽሙትንም ቢሆን ኢፖእአኮ ያወግዛል ።

አገዛዙ በሰፊው የህዝብን መብት ረገጣውን እንዲያቆም መደረግ አለበት ። ይህን እውን ለማድረግ ዜጎች ተባብረው ሊታገሉ ይጠበቃል ። ለሰብዓዊ መብት ቆመናል የሚሉ ብዙዎች የአንገት በላይ ነው መቆሮቆራቸው እንደታየው ከሆነ ። ሕዝብ ሲበደልና ሲረገጥ ማመጽ ግዴታው መሆኑ ደግሞ ክርክርን አይጠይቅም --ሰብዓዊ መብት በስጦታ አይገኝምና ። ብዙዎች ባለፉት ሳምንታት ተገድለዋል ፤ ወጣቶች ተቀጥፈዋል፡፡ ይህን ኢፖእአኮ ያወግዛል ። የሕዝቡንም ትግል ይደግፋል ። ካልታገሉ መብት አይከበርምና ። በሕዝብ መሃል ጥላቻ የሚያሰራጩትንም ኮሚቴው መቃውሙና ማጋለጡ ግዴታው ነው ። መሬት ንጥቂያ ያክትም፤ሕዝብን ማፈናቀል ይቁም ፤ የግድ ሰፈራ ይወገድ፤ በአጠቃላይም የመብት ረገጣው ቆሞ ሁሉም የፖለቲካና የፍትህ መጓደል እስረኞች ይፈቱ። ይህ ነው የህዝብ ጥያቄ፤ መስተጋባት መከርም ያለበት ጥያቄ ። የወያኔ ወዳጆች ሆነው በዕብሪቱና ግፉ ወደዱም ጠሉም ተባባሪ የሆኑትንም ደጋፊዎቹንም ጥብቅ ማሳሳቢያ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል ።

የህዝብ ህብረት ይጠንክር !!

በሕዝብ ላይ ግፍና ግድያው ይቁም !

መብት ረገጣው ያብቃ !!

ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ !!!\

**SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG, MB R2P 2Z7, CANADA**

**E MAIL: SOCEPP @AOL.COM**

**socepp@socepp.info/ WEB SITE: http://www.socepp.info**